DMU

**Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 8(2024) 1396-1415**

Journal homepage: www.ajids.com.et

AJIDS

**Volume 8(2), Dec 2024**

# ከሙሴ ታቦት መጥፋት ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት ጭብጦች ላይ የተደረገ ንጽጽራዊ ጥናት

Demisachew Shitaw[1]*, Mesfin Fekadie[2]

[1]Department of Chemistry, College of Natural and Computational Sciences, Debre Markos University, POB 269, Debre Markos, Ethiopia

[2]Department of Ethiopian Language and literature Amharic, College of Social Science and Humanities, Debre Markos University, Debre Markos, Ethiopia

*Coresponding Author email: Demisachew_shitaw@dmu.edu.et

## *አኅጽሮተ ጥናት*

*ይህ ጥናት "ከሙሴ ታቦት መጥፋት ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት ጭብጦች" ላይ የቀረቡ መረጃዎችን ይዳስሳል፡፡ የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያትም በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለዉ አንድነት እና ልዩነት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ነዉ፡፡ ምክንያቱም ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ የተለያዩ አመለካከቶች ይንጸባረቃሉ፡፡ ከነዚህ አመለካከቶች መካከል በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት መካከል ያለዉ ልዮነት አንዱ ነዉ፡፡ በመሆኑም ከሙሴ ታቦት ከሰሎሞን ቤተመቅደስ መጥፋ ጋር በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለዉን አንድነት እና ልዩነት በማስረጃዎች አስደግፎ ለማሳየት ያለ ፍላጎት የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓለማ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለዉን አንድነት፣ ልዩነትና የልዩነታቸውን ምክንያት በማሳየት የትኛዉ ጭብጥ ይበልጥ አሳማኝ እንደሆነ መግለጽ ነዉ፡፡ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር ተያይዞ ክብረ ነገስት እና ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት ምን ይላሉ? ሁለቱ መጻሕፍት በሙሴ ታቦት መጥፋት ላይ ምን ተመሳስሎና ልዩነት አላቸው? የሚሉት ናቸዉ፡፡ በጥናቱ ዉጤት መሰረት ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ ክብረ ነገስት እና ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት የሚያመሳስላቸዉ ጭብጥ የሙሴ ታቦት በኢትዮጵያ እንደምትገኝ መግለጻቸው ነው፡፡ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ከሚታዩ ልዩነቶች አንዱ የሙሴ ታቦት እንደ ክብረ ነገስት አገላለጽ በ935 (ቅድመ ልደተ ክርስቶስ) ታቦቷ ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ ወጥታ ቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣችና በትግራይ ደብረ ማክዳ እንዳረፈች ይገለጻል፡፡ በአንጻሩ በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ ደግሞ ታቦቷ በዘመነ ምናሴ በ670 ቅልክ አካባቢ ከሰሎሞን ቤተመቅደስ ወጥታ ግብጽ ኤሌፋንታይን ደሴት እንደተቀመጠች፣ በ470 ቅልክ አካባቢ ድግሞ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ጣና ቂርቆስ እንደመጣች፣ ከዚያ በ330 ዓ.ም በንጉስ አብርሃና አጽብሃ አማካኝነት ከጣና ቂርቆስ ወደ አክሱም እንደሄደች ያስረዳል፡፡ ሁለቱም መጻሕፍት የሙሴ ታቦት ከሰሎሞን ቤተመቅደስ መጥፋት ጋር ከሚያነሱት መሰረታዊ ጭብጥ አንጻር በዚህ ጥናት ዳሰሳ መሰረት የክብረ ነገስት አምክንዮ አሳማኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን ሙሴ በደብረ ሲና የተቀበለው ሁለት ጽላት ስለነበር ሁለቱ ጽላት ከሙሴ ታቦት ጋር ይሁን ወይንም ከሙሴ ታቦት አንደኛው ደግሞ ከአዛርያስ ታቦት ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥናት እንዲካሄድ ምክረ ሀሳብ በመስጠት ጥናቱ ተጠናቅቋል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡-** *የሙሴ ታቦት፣ ክብረ ነገስት፣ ታቦተ ጽዮን ፍለጋ*

**An Analytical Comparison of the themes in the Glory of Kings and the search for the Ark of Zion Concerning the Vanishing of Mose's Ark.**

***Abstract***

*This research explores the concepts depicted in the books of Kings and the search for the Ark of Zion concerning the Ark of Mose's. This investigation seeks to illustrate the similarities and distinctions found in the two books. The study used a qualitative approach to its investigation. The basic questions of the study are related to the disappearance of the Ark of Moses, what do you believe the books of the King and the Search for Ark of Zion? What are the similarities and differences between the two books on the disappearance of Moses' Ark? The data was analysed using comparative theory. Based on the study's findings, the books of Glory and Finding the Ark of Zion's topic on the Ark of Moses' absence is that they claim that the Ark is in Ethiopia. The Ark of Moses is one of the most significant changes between the two books. According to a Glory of Kings statement from 935 (Before to the birth of Christ), the Ark left Solomon's Temple, travelled straight to Ethiopia, and arrived in Tigray Debre Makda. In contrast, the Ark departed Solomon's Temple during the Minasie era, about 670 BC, and was positioned on Elephantine Island in Egypt, according to the book Search for the Ark of Zion. In terms of the basic theme that both books deal with the disappearance of the Ark of Moses, according to this research survey, the Glory of Kings assmution is found to be convincing. However, since there were two Arks that Moses received at Mount Sinai, the study was concluded by recommending that further research be conducted to confirm whether the two Arks came with Moses' Ark or one of Moses'Arks and Azariah's Ark came to Ethiopia.*

**Key words**: *The Ark of Covenant, The Glory of Kings, Finding the Ark of Zion.*

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት ጭብጦች ላይ የተነሱ ሀሳቦችን ንጽጽራዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም መተንተን ላይ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ነዉ።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የሙሴ ታቦት[3] መሰወር (መጥፋት) ምስጢር አለመገለጹ ከአስደማሚ ክስተቶች መካከል አንዱ ነው። ንጉስ ሰሎሞን 955 ከክርስቶስ ልደት በፊት (ቅልክ) አካባቢ ለቃል ኪዳኗ ታቦት ቤተመቅደስ ሰርቶ በክብር፣ በደስታና በእልልታ እንዳስቀመጣት ተመዝግቧል።[4] ከጥበበኛውና አስተዋዩ ንጉስ ሰሎሞን ሞት ስድስት መቶ ዓመታት በኂላ ከባቢሎን ምርኮ መልስ የቃል ኪዳኗ ታቦት መጥፋት በይፋ ታወቀ። *The second Temple was inferior to the First (Solomonic) Temple because of the absence of*

---

[3] የሙሴ ታቦት ወይም የቃል ኪዳኑ ታቦት ወይም ታቦተ ጽዮን ወይም የእግዚአብሔር ታቦት በመባል ይገለጻል።

በእንግሊዘኛ ቋንቋ The Ark of the Covenant, The Tabernacle of the Law of the God, The Ark of Testimony, The Holy ark, Zion, Lady Zion, Ark of God በማለት እንደሚገልጹት።

[4] 1ኛነገ. 8፣ 21

the Ark of the Covenant.[5] ንጉስ ሰሎሞን የሰራው የመጀመሪያው የቃል ኪዳን ታቦት ማደሪያ የነበረው ቤተመቅደስ በ587 ቅልክ በናቡከደነጾር አማካኝነት ከወደመ በኋላ በ517 ቅልክ መልሶ ተገንብቶ ቢጠናቀቅም የቃል ኪዳኗ ታቦት ስለሌለች ለአብዛኛው እስራኤላዉያን የሐዘን ምንጭ ሆኗል፡፡ ይህን የእምነትና የታሪክ መሰረት የሆነችውን የሙሴን ታቦት መጥፋት፤ መሰወር ወይም መውደም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያለዉ ነገር የለም፡፡ ታዲያ የቃል ኪዳኗ ታቦት የጠፋው መቼ ነው? የሚለዉ መሰረታዊ ጥያቄ ነዉ፡፡

ጥያቄዉን ለመመለስና ምስጢሩን ለመፍታት በዘመናት ሂደት ብዙዎች በርካታ ጥረት አድርገዋል፡፡ የአይሁድ የትውፊት መጻሕፍት የሆኑት ታልሙድ[6]፣ ሚሽናህ[7] እና 2ኛ መቃቢያን[8] መጻሕፍት የቃል ኪዳኗን ታቦት እስራኤል ውስጥ ከባቢሎን ወረራ በፊት መቀበሯን ስለፃፉ በባቢሎን ወረራ ጊዜ ከቤተመቅደሱ ጋር አብራ ወድማለች የሚሉ እሳቤዎች አሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በርካታ የከርሰ ምድር ቁፋሮዎች ተከናውነዋል፡፡ ነገር ግን የቃል ኪዳኗ ታቦት በእስራኤል ምድር ውስጥ መቀበሯን ወይም በዚያ መዉደሟን የሚያመለክት ፍንጭ አልተገኘም፡፡ በዚህ ምክንያትም የአይሁድ የትውፊት መጻሕፍት ተቀባይነት አጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያውያን የትውፊትና የታሪክ መጽሐፍ የሆነው ክብረ ነገስት (The Glory of Kings) እና የግራሃም ሐንኮክ የጥናት ውጤት የሆነው "The Sign and The Seal" የቃል ኪዳኗን ታቦት አድራሻ በኢትዮጵያ አክሱም መሆኑን ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን በሁለቱ መጻሕፍት መካከል የቃል ኪዳን ታቦቱ ከንጉስ ሰሎሞን ቤተመቅደስ በወጣበት ዘመንና በአወጣው ሰው፣ ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት መንገድ፣ ኢትዮጵያ በገባበት ዘመንና አክሱም በደረሰበት ጊዜ ሰፊ ልዩነት ይታያል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓለማ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለዉን አንድነት እና ልዩነት በማሳየት የትኛዉ ጭብጥ ይበልጥ አሳማኝ እንደሆነ መግለጽ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች፡- በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለውን አንድነት ማየት፣ ልዩነታቸውን በዝርዝር ማቅረብ፣ የልዩነታቸውን ምክንያት ማብራራትና ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የቀረበዉን መጻሐፍ ለይቶ ማሳየት የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የጥናቱ ፋይዳ ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ ለሚነሱ አከራካሪ ሀሳቦች ምላሽ መስጠት፤ ለተጨማሪ ምርምሮች መነሻ በመሆን ማገልገል ነው፡፡ ጥናቱ በሁለቱ መጻሕፍት የሙሴ ታቦትን በተመለከተ በተነሱ ጭብጥ ሐሳቦች ላይ የተገደበ ሲሆን ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መጻሕፍት በማጣቀሻነት ተጠቅሟል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ሥነዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ (qualitative) ምርምር ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ሚጠናው ጉዳይ በቁጥር ሊገለፅ የማይችል እና በቃላት አማካኝነት በመተንተን የሚቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ ዓይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህንን ያህል ተዛምዶ ወይም ልዩነት (varation) አላቸው ብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በቁጥር ዘዴ አይገልጹም፡፡ መረጃዎችን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድን ተከትሎ

[5] Miguel F. Brooks, 2000
[6] Miguel F. Brooks, p. 180
[7] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 167
[8] Bernard Leeman, 2010

ነው፡፡[9] በመሆኑም ይህንን የምርምር ዘዴ በመጠቀም ሁለቱ መጻሕፍት ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ የሚያነሱትን ጭብጥ አንድነት እና ልዩነት በንጽጽር ለማጥናት በሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በመለየት፣ በማደራጀት እና በመተንተን መሰረታዊ የአንድነት እና ልዩነት ጭብጦችን አነጻጽሮ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ መረጃዎችን በንጽጽር ለመተንተን ንጽጽራዊ ንድፍ ሃሳብ (Comparative theory) ተግባር ላይ ዉሏል፡፡ በሰነድ ፍተሸ የተዳሰሱ መረጃዎች በንጽጽራዊ ንድፈ ሀሳብ ተደግፈዉና ተተንትነዉ ቀርበዋል፡፡

## 2. የቃል ኪዳኑ ታቦት

የቃል ኪዳኑ ታቦት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድር የመጣው በሙሴ[10] አማካኝነት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እስራኤላውያን ከግብጽ የ430[11] ዓመት ባርነት ወጥተው ወደ ከነዓን በተጓዙበት ጊዜ በሲና በርሃ ሲንከራተቱ ሙሴ ከአምላኩ ጋር ለመገናኘት ወደ ሲና ተራራ ወጥቶ ሁለቱን ጽላት ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ከሲና ተራራ ወደ እስራኤላውያን ሲወርድ ሕዝቡ ተሰባስቦ ጣኦት ሲያመልኩ አግኝቷቸዋል፤ በዚህ ድርጊታቸው የተናደደው ሙሴ ጽላቶቹን ከእጁ ጥሎ እንደሰበራቸዉ ይገለጻል፡፡[12] እግዚአብሔር ሙሴን "ጽላት እንደፊተኞቹ አድርገህ ጥረብ፤ ጽሑፉን እኔ እጽፍባቸዋለሁ"[13] አለው፡፡ ጽላቱንም በታቦቱ ውስጥ ማስቀመጥ እንዳለበት ተነገረው፡፡[14] እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ጽላቶች ለመጠበቅና ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ በወርቅ ያጌጠ ከግራር እንጨት የተሰራ መሰወሪያ ወይም ማስቀመጫ ታቦት በእግዚአብሔር ምሪት ከነገደ ይሁዳ በሚሆን ባስልኤል በተባለ ሰው እጅ ተሰራ፡፡ የተሰራው ታቦትም ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፤ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል፤ ቁመቱ ደግሞ አንድ ክንድ ተኩል ሲሆን፤ ሁለት ሁለት በወርቅ ቀለበት የተሰሩ የመሸከሚያ መሎጊያዎች በሁለቱ ጎኖቹ ሲኖሩት፤ ሁለት ከወርቅ የተሰሩ የኪሩቤል ሥዕሎች በስርየት መክደኛው ላይ እንደነበሩት ይገለጻል፡፡[15] ሙሴ በታቦቱ ውስጥ ሁለቱንም ጽላቶች እንዳስቀመጣቸዉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡[16] እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስተምሮ ታቦት ማለት ማደሪያ፣ መታያ ወይም የክብሩ መገለጫ ዙፋን ነው፡፡[17]

ይህ ታቦት ወደ ሰው ልጅ ሕይወት የመጣበትን ክስተት ብርሃኑ ጎበና እንደሚከተለው ይገልጸዋል፤

> *የሰው ልጅ ተጨባጭ የሆነ፣ ሕሊናው የሚያርፍበት ቁሳዊ ነገር መፈለግ እግዚአብሔር መንፈሱንና ክብሩን በሚታዩና በሚጨበጡ ነገሮች ላይ እንዲገልጽ አድርጎታል፡፡ እስራኤል በቃል ብቻ የሚያናግረን አምላክ አንሻም፤ የምናያቸው በመካከላችን የሚመላለሱ አማልክትን ስሩልን እያሉ መሪዎቻቸውን ያስቸግሩ እንደነበርና በተግባርም ጣኦት አቁመው አምላካቸውን ክደው ጣኦት ያመልኩ*

[9] ያለው እንዳወቀ፣ 1998፣ 20
[10] ዘጸ 25፣ 10-22
[11] ዘጸ 12፣ 40-41 (215 ዓመት በዮሴፍ አማካኝነት በነጻነት የኖሩበት ዘመን ሲሆን 215 ዓመት ደግሞ ዮሴፍን የማያውቅ አዲስ ፈርኦን ከነገሰ በኋላ በባርነት የኖሩበት ዘመን ነው፡፡ በሌላ በኩል እንደ አይሁድ ትውፊት (አቆጣጥር) እስራኤላውያን በግብጽ ባርነት የኖሩበት 215 ዓመት ሲሆን ቀሪው 215 ዓመት አብርሃም በከነዓን መኖር ከጀመረበት አንስቶ ያዕቆብ ግብጽ እስከወረደበት ጊዜ ነው የሚሉ አሉ፡፡)
[12] ዘጸ. 32፣ 19
[13] ዘጸ. 34፣ 1
[14] ዘዳ.10፣ 2
[15] ዘጸ 25
[16] ዘዳ. 10፣ 1-5
[17] ብርሃኑ ጎበና፣ ገጽ 122

*እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዚህም የተነሳ እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት የቃል ኪዳኑን ታቦትና የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዝ የያዙ ሁለት ጽላቶች ሰጠው፡፡[18]*

በተጨማሪም አባ ጎርጎርዮስ ታቦትን በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

*ታቦት ከኦሪት ሕግና ከእስራኤል የነጻነት ሕይወት ጋር የተያያዘ ታሪክና የትመጣ አለው፡፡ እስራኤል በግብጽ በባርነት ሳሉ የአባቶቻቸውን እምነት ስላልረሱ 'የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ አድነን፤ ፍረድልን' በማለት ይማጸኑ ነበር፡፡ አምላክም ጸሎታቸውን ሰምቶ ከግብጽ የ430 ዓመት የባርነት ቀንበር ነጻ አወጣቸው፡፡ ከነጻነት በኋላ አምልኮታቸውን በግልጽና በነጻነት ያደርጉ ዘንድ በመሪያቸው በሙሴ አማካኝነት አስርቱ ትዕዛዛት የተጻፈባቸው ሁለት ሰሌዳዎችን (ጽላት) ሰጠው፡፡[19]*

ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለዉ ታቦት የጽላት ማደሪያ ሲሆን፤ እግዚአብሔር በደመና ሆኖ ሙሴንና አሮንን የሚያናግርበት ለእስራኤላውያን በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡[20] ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሲና ወደ ከነዓን፣ ከሴሎ ወደ አቤንኤዜር ከዚያም ወደ አዛጦን፣ አስቀሎና እንደገናም ለእስራኤል ልጆች ተመልሶ ወደ ሳሚስ፣ ከዚያም አሚናዳብ ቤት ሲቀመጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ሁኔታዉን ይተርካል፡፡[21] ቀጥሎም ከአሚናዳብ ቤት ወደ አቢዳራ ቤት ሲዛወር፣ ከዚያም ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ጽዮን አምባ ሲመጣ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተሰናስሎ ቀርቧል፡፡[22] ይህ ሁሉ ሲሆን፤ ሁለቱንም ጽላት እንደያዘ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሠርቶ (955 ቅልክ[23] አካባቢ) ወደዚያ እንዲገባ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ በድንኳን ውስጥ ይቀመጥ እንደነበር[24] መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የቃል ኪዳኗ ታቦት መኖር እስከ ንጉስ ሰሎሞን ድረስ ይናገሩ የነበሩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከርሱ በኋላ ፈጽሞ እንዳልነበረች ረስተዋታል፤ ታቦቷ ስለመጥፋቷ ወይም ስለመዉደሟ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተገለጸም፡፡ ምን እንደደረሰባት ወዴት እንደሄደች አናውቅም የሚል አስተያየት እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀመም፡፡ የእስራኤል የትውፊት መጻሕፍት ታቦቷ ከባቢሎን ምርኮ በፊት በኢዮስያስ ዘመን (ከ640-609 ቅልክ) በኢየሩሳሌም እንደተቀበረች ቢናገሩም በከርሰ ምድር ቁፋሮ ሀሳቡ ውድቅ ተደርጓል፡፡[25]

ክብረ ነገስት እና *ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ* የተባሉ መጻሕፍት የቃል ኪዳኗ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷን ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን ክብረ ነገስት በንጉስ ሰሎሞን ዘመን (971-931 ቅልክ) በቀዳማዊ ምኒልክ እና በአዛርያስ አማካኝነት በ935 ቅልክ አካባቢ ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ በፈቃደ እግዚአብሔር እንደመጣችና ትግራይ ውስጥ ደብረ ማክዳ እንዳረፈች ይገልጻል፡፡[26] የግራሃም ሐንኮክ ጥናት ውጤት የሆነው The Sign and The Seal በጌታቸው ተስፋዬ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ ተብሎ ከእንግሊዘኛ ወደ አማረኛ ተተርጉሟል፡፡ ይህ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ የሚለው መጽሐፍ የሙሴ ታቦተ ከሰሎሞን ቤተመቅደስ የወጣችው በንጉስ ምናሴ ዘመን (ከ687-642 ቅልክ) በሌዋውያን ካህናት ነው

[18] ብርሃኑ ጎበና፣ ገጽ 121
[19] አባ ጎርጎርዮስ፣ ገጽ 91-92
[20] አባ ጎርጎሪዮስ፣ ገጽ 93
[21] 1ሳሙ. 4፣ 1-4 እስከ ም. 7፣ 2
[22] 1ሳሙ. 6፣ 1-17
[23] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 159
[24] 1ኛ ነገ 8፣ 21
[25] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 172
[26] ስርግው ገላው፣ ገጽ 48

ይላል፡፡ የቃል ኪዳኗ ታቦት በግብጽ ኤሌፋንታይን ደሴት ለ200 ዓመታት (670 - 470 ቅልክ) ከቆየች በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሄዳ በጣና ቂርቆስ ደሴት ለ800 ዓመታት (470 ቅልክ - 330 ዓ.ም) ቆይታ አክሱም የደረሰችው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ330 ዓ.ም እንደሆነ[27] ይገልጻል፡፡ በክብረ ነገስት እና በግራሃም ሐንኮክ መካከል ታቦቷ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችበት ጊዜ የ500 ዓመታት ልዩነት አለው፡፡ ክብረ ነገስትና ግራሃም ሐንኮክ ታቦቷ ወደ ኢትዮጵያ በመጣችበት ዘመን፣ ባመጣት ሰው እና በመጣችበት መንገድ ሰፊ ልዩነት ይታያል፡፡ የቃል ኪዳኗ ታቦት አንድ ስለሆነች እና አንዴ ወደ ኢትዮጵያ ገብታ የወጣችበት ታሪክ ስለሌለ በሁለቱ ታሪኮች መካከል ያለው ልዩነት ከየት መጣ? ትክክለኛው የታሪክ እውነታ የትኛዉ ነው? የሚለዉ መሰረታዊ ጥያቄ የዚህ ጥናት ዋና የትኩረት አቅጣጫ ነዉ፡፡

## 3. የሙሴ ታቦት በክብረ ነገስት

ክብረ ነገስት ለ700 (1270-1974 ዓ.ም) ዓመታት ለኢትዮጵያ እንደ ህገ መንግስት ሆኖ አገልግሏል፡፡ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን በ1868 እንግሊዞች ከመቅደላ ዘርፈው ስለወሰዱት በ1872 ዓ.ም አጼ ዮሐንስ እንግሊዛዊዉን ኧርል ግራንቪል (Earl Granville) አፈላልጎ ይልክላቸው ዘንድ በደብዳቤ ጠይቀውት እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡[28] ክብረ ነገስት በውስጡ ስለመንግስት የስልጣን ምንጭ፤ በትረ ስልጣን መያዝ ስለሚገባቸዉ ሰዎች ማንነት፤ ስለባለስልጣናት ኃላፊነትና የስልጣን ድርሻ፤ ስለሕዝብ መብትና ግዴታ፤ በነገስታትና በሕዝብ መካከል ስላለውና መኖር ስለሚገባው ሕጋዊ ግንኙነት፤ ስለሃገሪቱ መሰረታዊ ሕጎች ወሰን፤ … ስለቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በዝርዝር ዘግቧል፡፡ ክብረ ነገስት በንጉስ ሰሎሞን ዘመነ መንግስት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ እንደተዘጋጀ፤ በንጉስ ላሊበላ ዘመን ከቅብጥ ወደ ዐረቢኛ መተርጎሙን፤ ከዚያም የአክሱሙ ንቡረ እድ ይስሐቅ በአጼ አምደ ጽዮን ዘመን (1289-1319 ዓ.ም) ከዐረቢኛ ወደ ግዕዝ ተርጉመውታል፡፡[29] የግዕዝ ክብረ ነገስት 117 ምዕራፎች የያዘ ቢሆንም፤ ንቡረ እድ ይስሐቅ አስፋፍተውና አዳዲስ ሐሳቦችን ጨምረው እንዳዘጋጁት በመግቢያው ላይ ተገልጾል፡፡ በሌላ በኩል በርናርድ ሌማን የተባሉ ተመራማሪ ክብረ ነገስትን በተመለከተ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፤

> *The Kibra Nagast was complied in about A.D. 1314 in Aksum. It consists of two intertwined main documents of roughly equal length and a short conclusion. The earliest part is a totally Israelite (i.e. pre-586 B.C.) document known as the Sheba-Menelik Cycle and appears to have been originally recorded in Solomon's reign. The second part, the Caleb Cycle, was probably written in about A.D. 520 on the eve of the Christian invasion of Jewish Yemen.*[30]

በአሁኑ ሰዓት በአቀራርብም በይዘትም ልዩነት ያላቸው የክብረ ነገስት ቅጅዎች እንዳሉ አስረጅዎች ያመላክታሉ፡፡[31] ይሁን እንጅ የመጀመሪያው ክብረ ነገስት ጸሐፊ፣

[27] Graham Hancock, pp 513-515
[28] Miguele F. Brooks, pp. xxiii-iv
[29] ደሴ ቀለብ፣ ገጽ 162
[30] Bernard Leeman, 2010
[31] Miguele F. Brooks, pp xix - xxvi

የተጻፈበት ቋንቋና የተጻፈበት ጊዜ አይታወቅም፡፡[32] ለዚህ ጽሑፍ ንጽጽር የዋለው ክብረ ነገስት ግን በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አማካኝነት ካርል ቤዞልድ (C. Bezold) የተባሉ ጀርመናዊ ከፓሪስ ቤተመጻሕፍት አግኝተው በዐረቢኛ ያሳተሙትን ከጀርመንኛ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በስርግው ገላው በ1994 የተዘጋጀው ባለ167 ገጽ መጽሐፍ ነው፡፡

ክብረ ነገስት ታቦተ ጽዮን የመጣችው በንጉስ ሰሎሞን ዘመን በበኩር ልጁ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት እንደሆነ በመግለጽ መነሻውን ንግስተ ሳባ ላይ ያደርጋል፡፡ ንግስተ ሳባ በሶስት ስሞች ትጠራለች፡፡ በክብረ ነገስት ማክዳ[33] ስትባል፤ በመጽሐፈ ነገስት ንግስተ ሳባ[34]፤ በወንጌል ደግሞ ንግስተ አዜብ[35] በመባል ትታወቃለች፡፡ በንግስት ሳባ ዘመን የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ነግሶ ነበር፡፡ በዚያን ዘመንም ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመላለስ ታምሪን የሚባል ነጋዴ ነበር፡፡[36] ንጉስ ሰሎሞን በታምሪን አማካኝነት ለንግስተ ሳባ የግብዣ ደብዳቤ ስለጻፈላት ልትገናኘው ወደ እስራኤል ሂዳ እንደነበር ድርሳናት ይገልጻሉ፡፡[37]

ንግስተ ሳባ ጥበብን ፍለጋ በንጉስ ሰሎሞን 7ተኛ ዓመት የንግስና ዘመን ወደ እየሩሳሌም ሄዳ[38] ለስድስት ወር አብራው በኢየሩሳሌም ቆይታለች፡፡[39] ንጉሱም ሴት ወዳድ[40] ስለነበር እንደደረሰባትና ቀዳማዊ ምኒልክን ጸንሳ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰች፤ ማይበላ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች፡፡[41] ስሙንም በይነ ልሃኪም (የብልህ ሰው ልጅ ማለት ነው) እንዳለችዉ[42] በሂደትም ወደ ምኒልክ ተቀየረ፡፡ ምኒልክ በ22 ዓመቱ ከኢትዮጵያ ወደ አባቱ እየሩሳሌም እንደሄደ፤ አባቱ ንጉስ ሰሎሞንም በደስታ ተቀበለው፡፡[43] ንጉስ ሰሎሞን የበኩር ልጁ የሆነውን ምኒልክን በእስራኤል ማንገስ ፈለገ፡፡[44] ምኒልክ ግን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንደሚፈልግ ለአባቱ ቁርጥ ሐሳቡን ነገረው፡፡[45] ንጉሱም ልጁን በአገሩ ላይ ለመሾም ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት በመቅረቱ የእስራኤል የበኩር ልጆች በምኒልክ ግራና ቀኝ ተሹመው መሄድ እንዳለባቸው ከመኳንቶቹ ጋር መከረ፡፡[46] እነሱም ንጉሱን መቃወም ስለማይቻሉ በሐሳቡ ተስማሙ፤ ከዚያ ልጁን ቀብቶ ለኢትዮጵያ ዳዊት ብሎ አነገሰው፡፡[47] ከዳዊት ጋር የካህኑ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስ ሊቀ ካህናት ሲሆን፤ ሌሎቹም እንደ ማዕረጋቸው ተሾሙ፡፡[48] ምኒልክ ከሳዶቅ ሕገ ኦሪትን ከአባቱ ከንጉስ ሰሎሞን ስርዓተ መንግስትን ተምሮ ከአባቱ ተሰናብቶ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የታቦተ ጽዮንን ልብስ ለምኖ ስለነበር በሊቀካህኑ ሳዶቅ አማካኝነት ተሰጠው፡፡ ነገር ግን ምኒልክን ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ የተወሰነባቸው የእስራኤል ልጆች አንድ ነገር መከሩ፡፡ እሱም፤ ታቦተ ጽዮንን ከቤተመቅደስ

[32] ስርግው ገላው፣ ገጽ ፳ - ፲፪
[33] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 17
[34] 1ኛ ነገ 10፣ 1-14 ፤ 2ኛ ዜና 9፣ 1-8
[35] ማቴ 12፣ 42
[36] ስርግው ገላው፣ ገጽ 13
[37] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደስላሴ፣ ገጽ 3
[38] ስርግው ገላው፣ ገጽ 32

[39] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 20
[40] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 32 ፤ ኅሩይ ወልደስላሴ፣ ገጽ 3
[41] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 24
[42] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 25 እና 28
[43] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 25
[44] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 31
[45] ስርግው ገላው፣ ገጽ 31
[46] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 33-34
[47] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 34
[48] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 40

አውጥተው ይዘው ለመሄድ ተስማሙ፡፡[49] ታቦተ ጽዮንንም በአዛርያስ አማካኝነት ከቤተመቅደስ አውጥተው ይዘዋት ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ ተከዜ ሲደርሱ ለንጉስ ምኒልክ የእስራኤል ልጆች ምስጥሩን ነገሩት፡፡ ንጉሱም በደስታና በእልልታ ከእስራኤል በኩሮች ጋር ታቦተ ጽዮንን ይዞ ደብረ ማክዳ ኢትዮጵያ እንደገባ[50] ክብረ ነገስት ያስረዳል፡፡ በዚህ ሂደት ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ገብታ በደብረ ማክዳ ተቀመጠች፤ እስከዛሬም በአክሱም ትገኛለች፡፡ ይህን የሚያጠናክር በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ የሚከወኑ ሐይማኖታዊና ትውፊታዊ ድርጊቶች ከኦሪት ሕግጋት ጋር አንድ ከመሆናቸው በተጨማሪ የሰሎሞን ሥርዎ መንግስት በክብረ ነገስት ከተጠቀሰው ውጭ መቼ እንደተጀመረ የሚያረጋግጥ ግኝት ማግኘት አለመቻሉ አልተቻለም፡፡

ነገር ግን ንግስተ ሳባንና ምኒልክን በተመለከተ የሚነሱ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የንግስተ ሳባ ታሪክ አፈ-ታሪክ ነው የሚለዉ ነው፡፡ ንግስተ ሳባ ግን በንጉስ ሰሎሞን ዘመን እንደነበረች በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾል፡፡[51] የንጉስ ሰሎሞንን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት አድርጎ እየተቀበሉና እያመኑ የንግስት ሳባን ታሪክ አለመቀበል ብዙ ርቀት የሚሰድ አመክንዮ አይደለም፡፡ ክብረ ነገስትንም ቢሆን ያለበቂ ማስረጃ አፈ-ታሪክ ነው ብሎ ማጣጣል ተገቢነት የለዉም፡፡[52] ንጉስ ሰሎሞን 700 ሚስቶችና 300 ዕቁባቶች እንደነበሩት ይታወቃል፡፡[53] ደብዳቤ ጽፎ ጥሪ አድርጎ ከሄደችለት ሴት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም ማለትም ተአማኒነት የለዉም፡፡[54] በተጨማሪም የፈላሻዎች (ቤተ እስራኤሎች በኢትዮጵያ) በሰሜን ኢትዮጵያ መኖር፣ በአክሱም የቀዳማዊ ምኒልክ መቃብር በመባል የሚታወቅ ስፍራ መገኘቱና የሰሎሞናዊ ስርዎ መንግስት በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ 1974 ድረስ የነበረ መሆኑ በታሪክ መመዝገቡ ለተነሳዉ ጭብጥ አስረጅ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡[55]

ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ ንግስተ ሳባ ኢትዮጵያዊት አይደለችም የሚለው ነው፡፡ የሳባ ቤተመንግስትና የመታጠቢያ ስፍራዎች በአክሱም መገኘት የንግስተ ሳባ ትክክለኛ ቦታ ኢትዮጵያ መሆኑን ለማሳየት በቂ ማስረጃ ነዉ፡፡ ከጥንታዊ የታሪክ ጸሐፊዎች መካከል ፍላቢየስ ጆሴፈስ፣ አርጌንና አባ ጀሮም ንግስተ ሳባ የላዕላይ ግብጽ (ይህ ቦታ ሱዳንን ጨምሮ የኢትዮጵያ አካል ነበር) ገዥ መሆኗን እንደዘገቡት ሐመረ ተዋሕዶ ላይ ተመዝግቧል፡፡[56] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን የወለደችው ንግስተ ሳባ ግዛቷ በደቡብ እስከ ማዳካስካር፣ በምስራቅ እስከ የመን፣ በሰሜን እስከ ኖባ፣ በምዕራብ እስከ ኒያንዛ እንደሚደርስና መቀመጫዋ አክሱም አጠገብ ሳባ ከሚባል ቦታ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡[57] ንግስተ ሳባ ማለት የሳባ ንግስት ማለት ነው፡፡ ይህንን የንግስተ ሳባ ሕልው መሆንንና የቀዳማዊ ምኒልክን ታሪክ እንዲሁም የንግስቷን ኢትዮጵያዊነት የሚክዱ ወይም የሚጠራጠሩ የውጭ ጸሐፊዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ኢትዮጵያውያንም በምዕራባዉያን መምህሮቻቸው ተጽዕኖ መውደቃቸውን

[49] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 46
[50] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 54
[51] 1ኛ ነገ 10፣ 1
[52] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 174
[53] 1ኛ ነገ 11፣ 3
[54] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ፣ ገጽ ፲
[55] Bernard Leeman, 2009
[56] ሐመረ ተዋሕዶ፣ ገጽ 111
[57] ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 7

የተመለከቱት ሥርግው ሐመረ ተዋህዶ ላይ የሚከተለዉን ሀሳብ አስፍረዋል፤

> *የሕዝቡን እውነት የሚሸር ተጨባጭ የሆነ የታሪክ ማስረጃ በሌለበት የሕዝቡን ትውፊት በመካድ እንዲሁም ጥፋትን ብቻ መፈጸም የታሪክ ሰው ድርሻ አይደለም፡፡ ለመገንባት እንጅ ለማጥፋት ምንጊዜም ቀላል ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያን ጥንታዊ ትውፊት አንካድ፤ ከእርሱ የተሻለ ስለጥንቱ የሚያስረዳ እስካሁን በቂ ማስረጃ የለም፡፡*[58]

ስለሆነም ታቦተ ጽዮን በቀዳማዊ ምኒሊክ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ በፈቃዷ በሌዋውያን ካህናት በእነ አዛርያስ አማካኝነት መጥታለች የሚለውን እውነት ሊያስተባብል የሚችል ተጨባጭ መረጃ የሌለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4. የሙሴ ታቦት በግራሃም ሐንኮክ ጥናት

ግራሃም ሐንኮክ እንግሊዛዊ ተመራማሪ ሲሆን፤ የቃል ኪዳኗን ታቦት አድራሻ ለማግኘት የሰራውን ምርምር "The Sign and The Seal"[59] በሚል በ600 ገጽ መጽሐፍ አውጥቶታል፡፡ ይህን መጽሐፍ ጌታቸው ተስፋዬ **ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ** በሚል ርዕስ ተርጎሞ አሳትሞታል፡፡ ለዚህ ጽሑፍ በዋናነት አገልግሎት ላይ የዋለው፤ ጌታቸው ተስፋዬ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ በማለት በሜጋ ማተሚያ ድርጅት በ1999 ዓ.ም የታተመው ባለ 258 ገጽ መጽሐፍ ነው፡፡

ግራሃም ሐንኮክ እንደሌሎች የምዕራባውያን ምሁራን ሁሉ የንግስተ ሳባን ሕልውናና ኢትዮጵያዊነትን መቀበል ይከብደዋል፡፡ ግራሃም ሐንኮክ ንግሰተ ሳባን ላለመቀበል እንደምክንያት የሚያነሳዉ ኢትዮጵያ በ1000 ዓመት ቅልክ በዚህ ደረጃ የመንግስት ስርዓት ሊኖራት አይችልም፤ ምክንያቱም አቢሲኒያዎች ያልሰለጠኑ ሰዎች ነበሩ[60] በሚል ምክንያት የተነሳ ነው፡፡ ምንም እንኳን በአክሱምና በአካባቢው የንግስተ ሳባና የቀዳማዊ ምኒልክ የቤተመንግስት ፍርስራሽ፣ የመቃብር ቦታና መሰል ነገሮች በከርሰ ምድር ቁፋሮ ቢገኙም[61]፤ ማረጋገጫ የሚሆን የጽሑፍ መረጃ (ክብረ ነገስት) ቢኖርም፣ ከዚያ ጊዜ የጀመረና ለ3ሺ ዘመን መቀጠል የቻለ የመንግስት ስርዓት (የሰሎሞን ሥርዎ መንግስት) ቢፈጠርም፤ ኢትዮጵያን ከጥንታዊ አይሁዶች ጋር አንድ የሚያደርጉ የግርዘት፣ የማንጻት፣ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት የመለየት፣ ቀዳሚት ሰንበትን የማክበር፣ የታቦት እና የመሳሰሉት ትውፊቶችና ሐይማኖታዊ ስርዓቶች ቢኖሩም በምሁራን ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት በቂ ሆነዉ የተገኙ አይመስልም፡፡

የምዕራቡ ዓለም ምሁራን ታቦተ ጽዮንን ለመፈለግ መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ አድርገው በሰሎሞን ዘመን ታቦቱ ቤተመቅደስ እንደገባ ሲያረጋግጡ፤ እንደወጣ ግን የሚያሳይ መረጃ የለም በማለት ውድቅ ያደርጋሉ፡፡ የዚህ አስተሳሰብ ውጤት የሆነው ግራሃም ሐንኮክ በንጉስ ሰሎሞን ዘመነ መንግስት የቃል ኪዳኗ ታቦቱ በቀላሉ ይወጣል የሚል እምነት የለውም፡፡ ስለሆነም ፍለጋውን ይቀጥላል፡፡ ከዚህ ጥበበኛ ንጉስ በኋላ ታቦቱ ከቤተ መቅደስ እንደወጣ የተናገረውና ሌዋውያን በቦታው ይመልሱት ዘንድ ያዘዘው ንጉስ ኢዮስያስ ነው[62] በማለት ግራሃም ሐንኮክ ጥናቱን ይጀምራል፡፡

---

[58] ሐመረ ተዋህዶ፣ ገጽ 112
[59] Graham Hancock, 1997
[60] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 173-4
[61] Bernard Leeman, 2009
[62] 2ኛ ዜና 35፣ 3-4 ፤ ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 176/180

ግርሃም ሐንኮክ ኢዮስያስ ይህን ይናገር እንጅ መቼ ከቤተመቅደሱ እንደወጣ ለማረጋገጥ ሌሎች መረጃዎችን አስሷል፡፡ በተለይ ከሰሎሞን በኋላ በሮብዓም ዘመን በ926 ቅልክ የግብጽ ፈርኦን ሺሻቅ ኢየሩሳሌምን ወርሮና ዘርፎ ቢሄድም ከዘረፋቸው ውስጥ ግን ታቦተ ጽዮን እንዳልነበረች ተረጋግጧል፡፡[63] ከፈርኦን ሺሻቅ በኋላ እስራኤል በ722 ቅልክ በአሶራውያን ተወርራ አስሩ የእስራኤል ነገድ በባርነት ወደ አሶር ተግዘዋል፡፡ ይህ ወረራ በ701 ቅልክ ከሰሜን እስራኤል ወደ ደቡብ ተሸጋግሮ የወቅቱ የይሁዳ ንጉስ ሕስቅያስ ለአሶር ንጉስ ለሰናክሬም ከቤተመቅደሱ ወርቅ መገበሩን እንጅ ሰናክሬም ቤተመቅደሱን መመዝበሩን የሚያሳይ ምንም ዓይነት መረጃ የለም፡፡[64] ስለሆነም ታቦቱን ከቤተመቅደሱ የሚያስወጣ ክስተት አልተፈጠረም ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው በ606 ቅልክ የነበረው የናቡከደነጾር እየሩሳሌምን ወርሮ እነዳንኤልንና ሰልስቱ ደቂቅን በግዞት ወደ ባቢሎን የወሰደበት ዘመን ነው፡፡ ናቡከደነጾር ለሁለተኛ ጊዜ በ598 ቅልክ ኢየሩሳሌምን ዘርፎ ንጉሳቸውን ኢዮአቄምን ማርኮ ወደ ባቢሎን ወረደ፡፡ ናቡከደነጾር እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ በ587 ቅልክ[65] ኢየሩሳሌምን ወርሮ ሰሎሞን ያስገነባውን ቤተመቅደስ ዘርፎና አውድሞ የሄደበት[66] እነነብዩ ሕዝቅኤል የተጋዙበት፤ ነብዩ ኤርሚያስ የተሰደደበት፣ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ይህን የመከራ ጊዜ እንዳያይ ለ66 ዓመታት በእንቅልፍ ያሳለፈበት ባሮክም ከጓደኞቹ ተነጥሎ የአባቶቹን መቃብር የጠበቀበት ክስተት ነው፡፡[67] ይህ ዘመን እስራኤላዉያን በባቢሎናውያን ተግዘው ለ70 ዓመታት ከተገዙ በኋላ የፋርሶች የበላይነት ሲመጣ በ538 ቅልክ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል፡፡[68] የፋርስ መንግስት ቂሮስ ከእስራኤል ጋር የነበረው ግንኙነት ጥሩ ስለነበር በባቢሎናውያን የተዘረፉትን ሃብት በሙሉ ተመልሶላቸው ወደ አገራቸው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ታቦተ ጽዮን አለመኖሯን ድርሳናት ይገልጻሉ፡፡[69]

እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ቤተመቅደሱን እንደገና በ537 ቅልክ ግንባታ ጀምረው በ517 ቅልክ ሲጨርሱ ታቦተ ጽዮንን ወደ አዲሱ ቤተመቅደስ ማስገባት አልቻሉም፡፡[70] ይህ የሚያመለክተው ታቦተ ጽዮን ወደ ባቢሎን በምርኮ በወረዱት ሌዋውያን ካህናት እጅ አልነበረችም፡፡[71] ይህ ማለት ታቦተ ጽዮን ከእጃቸውም የወጣች ከባቢሎናውያን ወረራ በፊት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ከባቢሎናውያን በፊት ከ640-609 ቅልክ ጊዜ ንጉስ ኢዮስያስ ታቦቱ በቤተመቅደሱ እንዳልነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ተገልጾል፡፡[72] በሌላ በኩል ደግሞ ታቦቱ በቤተመቅደስ እንደነበር ለመጨረሻ ጊዜ የተገለጸው በሕዝቅያስ ዘመን (በ701 ቅልክ) እንደሆነ ግራሃም ሐንኮክ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ይሞግታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በሕስቅያስ ዘመን ታቦቱ ስለመኖሩ በግልጽ አይናገርም፡፡ ይሁን እንጅ የሕስቅያስ ጸሎት እንዲህ ይላል፡-

> *ሕዝቅያስም ደብዳቤውን ከመልእክተኞች እጅ ተቀብሎ አነበበው፤ ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር*

---

[63] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 162፤ 2ኛ ዜና 12፣ 2-9
[64] 2ኛ ነገ 18፣ 14-16
[65] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 164
[66] ዳንኤል ክብረት፣ ገጽ 8
[67] ወንጌል ቅዱስ፣ ገጽ 469-471
[68] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 165
[69] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 186
[70] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 165
[71] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 164
[72] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 176 /180

> *ፊት ዘረጋው፤ ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ጸለየ "በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ የእስራኤል አምላክ አቤቱ አንተ ብቻህን የምድር ነገስታት ሁሉ አምላክ ነህ፤ ሰማይና ምድርን ፈጥረሃል። አቤቱ ጆሮህን አዘንብልና ስማ፤ አቤቱ ዓይንህን ክፈትና እይ፤ በሕያው አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድ የላከውን የሰናክሬምን ቃል ስማ፤ … አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆንህ ያውቁ ዘንድ ከአሶር ንጉስ እጅ አድነን።"[73]*

እንደ ግራሃም ሐንኮክ ገለጻ ሕዝቅያስ ደብዳቤውን በታቦቱ ላይ እንደዘረጋው እንዲሁም በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ ብሎ የጸለየ ታቦቱ ስለነበር ነው። ይኸ ብቻ አይደለም፣ ንጉስ ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ተመስክሮለታል። በዚህም የተነሳ በእርሱ ዘመን ታቦቱ ከቤተመቅደስ ይወጣል ማለት ተገቢነት የለውም። በሕዝቅያስ ዘመን ታቦቱ በቤተመቅደስ ነበር ብሎ ማጠቃለል ተገቢ ነው ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በኪሩቤል ላይ እንደሚያድር፣ በታቦቱ ላይ እንደሚገለጥና ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየ ስለሚናገር በ701 ቅልክ ታቦቱ በቤተመቅደስ ውስጥ ነበር ብሎ ይገልጻል። ይሁን እንጅ ከሕዝቅያስ በኋላ በሶስተኛነት የነገሰው የኢዮስያስ ዘመን ከመግባቱ በፊት ታቦቱ ከቤተመቅደስ ውስጥ ጠፋ።[74] ይህን ማወቅ የምንችለው ኢዮስያስ ለካህናት በተናገረው መልዕክት አማካኝነት ነው። ኢዮስያስ ስለጉዳዩ እንዲህ ይላል፡

> *ቅዱሱን ታቦት የእስራኤል ንጉስ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በሰራው ቤት ውስጥ አኑሩት፤ ከዚህም በኋላ በትክሻችሁ ላይ ሸክም አይሆንባችሁም፤ አሁንም አምላካችሁን እግዚአብሔርንና ሕዝቡን እስራኤልን አገልግሉ።[75]*

በዚህ መልዕክት ውስጥ "አኑሩት" የሚለው ቃል ታቦቷ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳልነበረች ያመለክታል። ታቦቷ በቤተመቅደስ ውስጥ ብትኖር ኖሮ "በትክሻችሁ ላይ ሸክም አይሁንባችሁ" በማለት ባልተናገራቸው ነበር። ታቦቷ ከቤተመቅደስ ልትወጣ የምትችለው በሕዝቅያስ እና በኢዮስያስ መካከል ባለው ጊዜ ነው። ይህም ከ687 እስከ 640 ቅልክ ሲሆን 47 ዓመታትን ይይዛል። በሁለቱ ነገስታት መካከል የነገሱ ደግሞ ምናሴና አሞጽ ብቻ ናቸው። ምናሴ ለ45 ዓመት (ከ687-642 ቅልክ) ሲነግስ አሞጽ ግን ለሁለት ዓመት (ከ642-640 ቅልክ) ብቻ ነግሶ ሞቷል[76] (በመጽሐፍ ቅዱስ ግን የምናሴ የስልጣን ዘመን 55 ዓመት ነው)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለምናሴ እንዲህ ይላል፤

> *ምናሴ በነገሰ ጊዜ 12 ዓመት ሆኖት ነበር። በኢየሩሳሌምም 55 ዓመት ነገሰ። … እንደ አሕዛብ ርኩሰት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን አደረገ፤ አባቱም ሕዝቅያስ ያፈረሳቸውን የኮረብታውን መስገጃዎች መልሶ ሰራ፤ የእስራኤል ንጉስ አክዓብ እንዳደረገው ለበአል መሰዊያ ሰራ፤ የማምለኪያ ዐጸድንም ተከለ፤ ለሰማይ ሰራዊት ሁሉ ሰገደ፤ አመለካቸውም፤ እግዚአብሔርም "ስሜን በኢየሩሳሌም አኖራለሁ" ባለው በእግዚአብሔር ቤት መሰዊያዎችን ሰራ፤ ልጁንም በእሳት ሰዋ፤ ሞራ ገላጭም ሆነ፤ አስማትም አደረገ፤ አስቆጣውም፤*

[73] 2ኛ ነገ 19፣ 14-19

[74] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 177

[75] 2ኛ ዜና 35፣ 3

[76] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 183

> *.... በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት ክፉ ይሰሩ ዘንድ ምናሴ አሳታቸው፡፡*[77]

በምናሴ ክፉ ስራዎች ምክንያት እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ከባድ ቅጣት አወረደ፡፡ እግዚአብሔርም ተዋቸው፤ ታቦቷም በዚህ ዘመን ከእየሩሳሌም በታማኝ ሌዋውያን ካህናት አማካኝነት ተወሰደች፡፡ ታቦቷን ከጣኦት ጋር በቤተ መቅደስ መቀመጡን ካህናት አልፈቀዱም፡፡ የንጉሱን በትር ተቋቁመው ጣኦት በቤተመቅደሱ እንዳይገባ ማድረግ አልተቻላቸውም፡፡ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ በንጉሱ የማይፈለገውን ታቦት ይዘው መሰደድ ነው፡፡ የታቦቷ ጉዞ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ ግራሃም ሐንኮክ የተከተለው ንጉስ ኢዮስያስን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን ነው፡፡ ንጉስ ኢዮስያስ በመጀመሪያ ቤተመቅደሱንና አገሪቱን ከጣኦት አጸዳት፤ የፋሲካ በዓልን በእስራኤል ታሪክ ተከብሮ በማይታወቅ ድምቀት አከበረ፡፡ ከፋሲካ በዓል በኋላ በፈርኦን ኒካዑ ላይ ጦሩን ይዞ እንደዘመተ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል፡፡ ኒካዑ ኢዮስያስን

> *... የይሁዳ ንጉስ ሆይ፣ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? በምዋጋበት በሌላ ቤት ላይ ነው እንጅ በአንተ ላይ አልመጣሁም፤ እግዚአብሔርም እንድቸኩል አዝዞኛል፤ ከእኔ ጋር ያለው እግዚአብሔር እንዳያጠፋህ ይህን በእርሱ ላይ ከማድረግ ተመለስ፤ ...*[78]

ኒካዑ ለኢዮስያስ የተናገረው የእስራኤላውያን አምላክ ከእርሱ ጋር እንደሆነ አድርጎ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የእስራኤላውያን ልምድ ነው፡፡ እስራኤሎች ታቦቱ ከእነሱ ጋር በነበረበት ጊዜ ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽሙ ነበር፡፡ እንደ ግራሃም ሐንኮክ ከሆነ ኢዮስያስ ታቦቱን ከግብጽ ወደ እየሩሳሌም ለመመለስ ካለው ሐሳብ የተነሳ የኒካዑን ምክር ሰምቶ መመለስ አልፈለገም፡፡ ከግብጾች ጋር ጦርነት ገጥሞ በጦር ተወግቶ ሞተ፡፡[79] ኢዮስያስን ለሞት የዳረገው ጦርነት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተጠቀሰ ባይሆንም ከኒካዑ ንግግር መረዳት የሚቻለው ግን የእስራኤላውያን አምላክ ከእርሱ ጋር ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ታቦቱ ከእርሱ ጋር ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን የተረዳው ኢዮስያስ በእየሩሳሌም ቤተመቅደሱን ከጣኦት አጽድቶና ፋሲካውን ልዩ በሆነ ድምቀት አክብሮ በመጨረሻ ታቦቱን ወደ ቦታው ለመመለስ እንቅፋት የሆነውን ኒካዑን ሊወጋ ወጣ፡፡ ስለሆነም ታቦቱ በምናሴ ዘመን ወደ ግብጽ ወርዶ እንደነበር መገመት ቀላል ነው ይላል ግራሃም፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ሌዋውያን ካህናት በንጉስ ምናሴ ዘመነ መንግስት በቤተመቅደሱ ውስጥ ጣኦት በመግባቱ የተነሳ የቃል ኪዳኗን ታቦት ከቤተመቅደሱ ውስጥ በማውጣት ራቅ ወዳለ ቦታ መውሰድ ነበረባቸው፡፡ ለዚህ ተመራጭ የሆነችው ግብጽ ነች፡፡ ለዚህ ማስረጃ በግብጽ አስዋን አጠገብ ኤሌፋንታይን ደሴት ላይ በ670 ቅልክ ተገንብቶ የነበረው የአይሁድ ቤተመቅደስ ነው፡፡ ቤተመቅደሱ የሰሎሞን ቤተመቅደስን እንደሚመስልና እንደሚያክል (27 ሜ ርዝመት እና 10 ሜ ወርድ)[80] የከርሰ ምድር ጥናት ያመለክታል፡፡ አይሁዳውያን ባቢሎን ለ70 ዓመታት በግዞት ሲቀመጡ ቤተመቅደስ አልገነቡም፡፡ ቤተመቅደስ ከእየሩሳሌም ውጭ መገንባትም የተከለከለ ነበር፡፡ ታዲያ ለምን በግብጽ ኤሌፋንታይን ደሴት ላይ የአምልኮ

[77] 2ኛ ነገ 21፣ 1-9
[78] 2ኛ ዜና 35፣ 21
[79] 2ኛ ዜና 35፣ 23-24
[80] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 195

ቤተመቅደስ ልክ የሰሎሞንን አስመስለው በ650 ቅልክ ሊገነቡ ቻሉ? የሚለው ጥያቄ መልሱ በእጃቸው ታቦተ ጽዮን ስለነበረች ነው የሚለው በብዙ መስፈርቶች አሳማኝ ይሆናል፡፡[81] በኤሌፍንታይን የነበረው የአይሁድ ማህበረሰብ ያካሂድ የነበረው የእንሰሳት መስዋዕት ከንጉስ ኢዮስያስ አዋጅ በኋላም ሳይቋረጥ የቀጠለው ታቦቱ በእጃቸው ስለነበር መሆኑን ያሳያል፡፡[82]

እንደጥናቱ የአይሁዶች በግብጽ የነበራቸው ቆይታ ለ200 ዓመት (ከ670-470 ቅልክ) አካባቢ ነበር፡፡ በግብጾች አማካኝነት በኤሌፋንታይን ደሴት የነበረው የአይሁድ ቤተመቅደስ በ410 ቅልክ ተደመሰሰ፡፡ በቦታው ይኖሩ የነበሩ አይሁዶችም ከቦታው ተሰደው ጠፉ፡፡ ይህ የሆነው የፋርሶች የበላይነት በግብጾች ሲተካ ነው፡፡ ግብጾች የበላይነታቸውን ሲያገኙ በሁለት ምክንያቶች ከእስራኤላውያን ጋር ተጣሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት እስራኤላውያን ከፋርሶች ጋር ተባብረው ስለነበር አሁን ፋርሶች ሲመቱ እነሱም ተመሳሳይ እጣ ፋንታ ገጠማቸው፡፡ ሁለተኛው አይሁዶች በቤተመቅደሳቸው ይሰውት የነበረው የበግ ጠቦት የግብጾች የጣኦት አምላክ ምልክት ስለነበር ግብጾች በጠላትነት ተነሱባቸውና አሳደዷቸው፡፡[83] በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ከላይኛው ግብጽ ተነስተው በታችኛው ግብጽ አልፈው ወደ አገራቸው ከነዓን መመለስ አይችሉም፡፡ ግብጾች ያጠፏቸዋል፤ ስለሆነም የናይልን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ በጣና ደሴቶችና በጎንደር ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ተቀመጡ፡፡ ታቦቱንም በጣና ቂርቆስ ደሴት ድንኳን ውስጥ አስቀመጡት፡፡ ይህን በጣና ደሴት በሚገኙና ከታቦቱ ጋር በመጡ ንዋየ ቅድሳት፣ ታቦቱ አርፎበት የነበረ ቦታ እና በገዳሙ አባቶች ትውፊታዊ ትምህርት በማመሳከር እውነትነቱን ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡[84]

በጣና ቂርቆስ ገዳም የደም መሥዋዕቱ በሌዋውያን ካህናት ከዘመናት በፊት ይቀርብበት የነበረን ቦታ ከማየቱ በተጨማሪ ከታቦቱ ጋር የመጡ እስካሁን ድረስ በጣና ቂርቆስ ገዳም የሚገኙ ንዋየ ቅድሳት መካከል ጎሜር[85] (ትልቅ ጎድጓዳ ሰሐን) እና የብረት መቋሚያ (የትልቁ ጎድጓዳ ሰሐን ማስቀመጫ) እንዳለ ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ዕቃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ለልዩ ልዩ አገልግሎት እንደሚዉሉ ተጠቅሶል፡፡[86] ታቦቱን ይዘው የመጡት የአይሁድ ካህናት በደሴቲቱ ላይ የተውት የስጋ ሹካ (በእሳቱ ላይ የሚቃጠለውን መስዋዕት ለማገላበጥ የሚረዳ) እና የአሮን በትር (በሙሴ ዘመን በቤተ መቅደስ በተአምራት ለምልማ፣ አብባና አፍርታ የተገኘችው)[87] ይገኛሉ፡፡ እነዚህን መሰረት በማድረግ ታቦቱ በጣና ቂርቆስ ገዳም እንደነበር መግለጽ ይቻላል፡፡ የሃይማኖት መሪ የሆኑ አረጋዊ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ከመሄዱ በፊት ለ200 ዓመት ግብጽ ስለመቀመጡ ይናገራሉ፡፡ በጣና ቂርቆስ ገዳም ለ800 ዓመት እንደነበር ያምናሉ[88]፤ የኢየሩሳሌም አይሁድ ኢንስቲቲዩት ተመራማሪ የሆኑት ሻሊቭ ዊል ከዘመናት በፊት ታቦቱን ይዘው ግብጽ የወረዱት ካህናት በግብጽ ለተወሰነ ወቅት ከቆዩ በኋላ

[81] ሣህለ ጥላሁን፣ ገጽ 241-42 ፤ ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 191-95

[82] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 195፣ 99

[83] ሣህለ ጥላሁን፣ ገጽ 241-42 ፤ ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 196/200

[84] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 114-17፤ ሣህለ ጥላሁን፣ ገጽ 218-27

[85] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 116

[86] ዘጸ. 30፣ 17-19 እና 26 ፤ ዘሌ. 8፣ 10-11

[87] ዘኁ. 17፣ 8

[88] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 115

ወደ ኢትዮጵያ እንደሄዱ ታቦቱም በዚህ ሂደት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገባ ይገልጻል፡፡[89] ስለሆነም የዓባይን ወንዝ ተከትለው ከግብጽ የመጡ አይሁዳውያን ታቦት ይዘው ወደ ጣና ቂርቆስ ገብተው 800 ዓመት አካባቢ በአይሁድ እምነት ስርዓት እንደኖሩና በዘመነ ክርስትና በተለይ በአብርሃና አጽብሃ ዘመነ መንግስት ታቦቱ ወደ አክሱም እንደሄደ ያረጋግጣል፡፡[90] በዚህም ከረጅም ጊዜ ምርምር በኋላ ታቦተ ጽዮን አክሱም እንደምትገኝ አስታወቀ፡፡[91] ሣህለ ጥላሁን "ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን?" ብሎ በተረጎመው የአሜሪካዊው ሮበርት ኮርኑክ "Relic Quest"[92] መጽሐፍ ከግራሀም ሐንኮክ የምርምር ውጤት ጋር ተመሳሳይ ውጤት ማግኘቱን እና አክሱም በነበረበት የመጨረሻ ጉዞው "… በቃል ኪዳኑ ታቦት ጥላ ስር መቆሜን አረጋግጫለሁ"[93] በማለት አጠቃሎታል፡፡

## 5. የሁለቱ መጻሕፍት የልዩነት ምክንያት

ከላይ ማየት እንደታቻለው ክብረ ነገስትና ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት የሙሴ ታቦት ከሰሎሞን ቤተመቅደስ ወጥታ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደምትገኝ ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን የሙሴ ታቦት ከሰሎሞን ቤተ-መቅደስ በወጣችበት ዘመን፣ ወደ ኢትዮጵያ በመጣችበት መንገድና አክሱም በደረሰችበት ዘመን ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡ የዚህን የልዩነት ምክንያት ከራሳቸው ከሁለቱም መጻሕፍት ድምዳሜዎች እናገኛለን፡፡

[89] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114-15፤ ሣህለ ጥላሁን፣ ገጽ 233
[90] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 200
[91] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 245-46
[92] Robert Cornuke, Relic Quest (በሣህለ ጥላሁን ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን? ተብሎ በአማርኛ ተተርጉሟል)
[93] ሣህለ ጥላሁን፣ ገጽ 310

በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ ላይ በኤሌፋንታይን ለ200 ዓመት የኖሩት አይሁዳውያን ከግብጽ ለመውጣት ሲገደዱ ምርጫቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉት በዘፈቀደ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ወደ እስራኤል መመለስ መንገዳቸው ከባድ የሚሆንባቸው መሆኑን ቢያውቁም፤ ጉዞአቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉት በአጋጣሚ ሳይሆን እነሱን በደምና በእምነት የሚመስሉ ቀደምት አያቶቻቸው በኢትዮጵያ ስለነበሩ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ የአይሁድ ቅድመአያቶች መቼና እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ገቡ? የሚለውን ጥያቄ በእርግጠኝነት ባይናገርም ከኢሳይያስና ሶፎንያስ ትንቢቶች በመነሳት ከንጉስ ኢዮስያስ በፊት ወደ ኢትዮጵያ የገባ የአይሁድ ማህበረሰብ እንደነበር ዘግቧል፡፡[94] ለመሆኑ ከንጉስ ኢዮስያስ ዘመን (ከ640-609 ቅልክ) በፊት የአይሁድ ማኅበረሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሰደድ የሚያደርገው ክስተት ተፈጥሮ ነበር? ከተፈጠረስ መቼ?

ለዚህ ጥያቄ መልስ የታሪክ ሰነዶችን እንመልከት፡፡ እንደ መጽሐፈ ነገስት አቆጣጥር እስራኤላውያን ከግብጽ በሙሴ አማካኝነት ከወጡበት እስከ ሰሎሞን ድረስ ያለው ዘመን 480 ዓመት ነው፡፡[95] በዚህ ሂደት እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው በአንድነት ወደ ርዕስታቸው የሄዱበት፣ ከአምላካቸው የቃል ኪዳን ታቦት በሲና በርሃ የተቀበሉበት፣ ሙሴን በተካው በኢያሱ አማካኝነት ጠላቶቻቸውን ድል አድርገው በነገድ ርስት የተከፋፈሉበት፣ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በርካታ ውጊያዎች ያደረጉበት፣ አልፎ አልፎም በሌሎች ቅኝ ግዛት የወደቁበት[96]፤ ከመሳፍንት ግዛት ወደ

[94] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 201-212
[95] 1ኛ ነገ. 6፣ 1
[96] ዳንኤል ክብረት፣ ገጽ 139-140

ንጉሳዊ ስርዓት የተሸጋገሩበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን አገራቸውን ትተው ወደሌላ አገር በተለይ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱበት (የተጋዙበት) አጋጣሚ አልተመዘገበም፡፡

ሁለተኛው በንጉስ ሰሎሞን ዘመነ መንግስት በክብረ ነገስት ከተመዘገበው የእስራኤል የበኩር ልጆች ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከካህናትና ከመኳንንት ልጆች 23 ታላላቆችን ሾሞ 12000 የአዋቂዎችና የብልሆች የበኩር ልጆች ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ አስረስ የኔሰው በመጥቀስ ደሴ ቀለብ ዘግቦታል፡፡[97] ይህ ማለት ከኢዮስያስ ዘመን በፊት በ935 ቅልክ አካባቢ አይሁዳውያን ወደ ኢትዮጵያ ታቦተ ጽዮንንና የኦሪት መጻሕፍትን ይዘው ገብተዋል፡፡

ሶስተኛው ጊዜ እስራኤል ለሁለት ከተከፈለችበት 930 ቅልክ እስከ ኢዮስያስ ዘመን ያለው ነው፡፡ እስራኤል በሮብዓምና በኢዮርብዓም አማካኝት ለሁለት መከፈሏ በተለይ ሁለቱን ነገድ የያዘው ደቡብ እስራኤል በፈርኦን ሺሻቅ (926 ቅልክ) አማካኝነት ስትዘረፍ አልተሰደዱም እንጅ ቢሰደዱም ወደ ኢትዮጵያ ሳይሆን ወደ ሶሪያና ባቢሎን ይሆን ነበር፡፡ ሁለተኛው ክስተት አስሩን ነገድ የያዘው ሰሜን እስራኤል ዋና ከተማ ሰማርያ በአሶራዉያን የተያዘችበት ዘመን 722 ቅልክ ሲሆን በ701 ቅልክ የአሶር ንጉስ (ሰናክሬም) ይሁዳን ለመያዝ ያደረገው ጥረት አልተሳካለትም፡፡[98] በዚህ በከሸፈ ወረራ ምንም እንኳን ሰሜኖች ወደ ደቡቦች የተሰደዱ ቢሆንም፤ ከደቡብ የእስራኤል ክፍል ግን ስደት የሚያስወጣ ክስተት አልነበረም፡፡ በዚህ ጊዜ አይሁዳውያን አገራቸውን ትተው ኢትዮጵያ ድረስ ይሰደዳሉ ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ከዚህ ውጭ ስደት ያስከተለ ችግር በእስራኤላውያን ላይ የደረሰው በናቡከደነጾር አማካኝት በ587 ቅልክ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከኢዮስያስ ዘመን በኋላ የተከሰተ ነው፡፡

በግራሃም ሐንኮክ ግኝት ከኢዮስያስ ዘመን በፊት ተሰዶ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሕዝብ አለ በማለት የተጠቀሰው በክብረ ነገስት የተመዘገበውን የሕዝብ ከምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መግባት መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ውጭ በማስረጃ የቀረበ ታሪክ የለም፡፡ ግራሃም ሐንኮክ እንደጠቀሰው በኢትዮጵያ ያሉት አይሁዶች ከንጉስ ኢዮስያስ በፊት የመጡ ስለመሆናቸው ልዩ ልዩ ማሳያዎች ቢኖሩም አንዱን እንጥቀስ፡፡ በንጉስ ኢዮስያስ ዘመነ መንግስት ማንኛውም አምልኮትና መስዋዕትነት መቅረብ ያለበት በእስራኤል በቤተመቅደሱ ብቻ መሆን እንዳለበት ተወስኗል፡፡ ባቢሎን የወረዱት እስራኤላውያን "ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን"[99] አሉ እንጅ በባዕድ አገር ምንም ዓይነት መስዋዕት አላቀረቡም፡፡

ፈላሾች በንጉስ ኢዮስያስ ዘመን ስለተጻፈው ታልሙድና የታልሙድ ሕግ የሚያውቁት ነገር የላቸውም፡፡[100] ከኢዮስያስ ዘመን በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ የአይሁድ ማኅበረሰብ እንደነበር ማሳያ ነው፡፡ ሌላው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት አንድ መሰረታዊ ቁም ነገር አለ፡፡ እሱም አይሁዶች በስደትም ሆነ በግዞት በሄዱባቸው አገሮች ማለትም ግብጽ፣ አሶር፣ ባቢሎንና ፋርስ ባህላቸውንና እምነታቸውን ልክ እንደ ኢትዮጵያ የአገሩ ባህል ማድረግ አልቻሉም፡፡ የኦሪት ሕግና ስርዓት መሬት መያዝ የቻለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ለምን? ምክንያቱም ንግስተ ሳባ ከንጉስ

[97] ደሴ ቀለብ፣ ገጽ 101 ሕዳግ

[98] 2ኛ ነገ 17፣ 23 ፤ ቸርነት አበበ፣ ገጽ 40

[99] መዝ 137፣ 1

[100] Miguele F. Brooks, p. 180

ሰሎሞን ጋር በፈጠረችው መልካም ግንኙነት ቀዳማዊ ምኒልክ ተወለደ፡፡[101] ቀዳማዊ ምኒልክ ከአባቱ ከንጉስ ሰሎሞን መንግስታዊ ስርዓትን እንዲሁም ከሊቀ ካህኑ ሳዶቅ የኦሪት ስርዓትን በኢየሩሳሌም ተማረ፡፡[102] ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ በእስራኤላውያን አማካኝነት ሕገ ኦሪትንና ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ከታቦተ ጽዮን ጋር ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡[103] እንደ ክብረ ነገስት ገለጻ ይህ ክስተት እንዲህ በቀላሉ የተከናወነ አይደለም፡፡ ንጉስ ሰሎሞን ልጁን ምኒልክን አንግሶ በመንበሩ ላይ ያስቀምጠው ዘንድ ወደደ፡፡[104] ምኒልክ ግን በኢየሩሳሌም የአባቱ ተተኪ ንጉስ ለመሆን አልፈለገም፡፡ ይልቁንም ወደ አገሩ ይመልሰው ዘንድ አባቱን ተማጸነ፡፡ ንጉስ ሰሎሞን የበኩር ልጁን በእየሩሳሌም ማስቀረት አለመቻሉን ሲያውቅ ብቻውን ይመለስ ዘንድ አልፈቀደም፡፡ የእስራኤል የበኩር ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ምኒልክን ተከትለው መሄድ እንዳለባቸው ንጉሱ አሰበ፡፡ ከመኳንንቶቹ ጋር መከረ፡፡ በእስራኤል ምድር የበኩር ልጅ የሆነ ሁሉ አብሮ ከምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ተወሰነ፡፡ የሊቀ ካህኑ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስም ወደ ኢትዮጵያ ከሚሄዱት መካከል ሆነ፡፡ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ የተወሰነባቸው የበኩር ልጆች በተለይ ከታቦተ ጽዮን ተለይተው መሄዳቸውን ሲያስቡ አዘኑ፡፡ ታቦተ ጽዮንን የሚያስታውሱበትና አምላካቸውን የሚያመልኩበት ነገር ይሰጣቸው ዘንድ ጠየቁ፡፡

ንጉስ ሰሎሞን የታቦተ ጽዮንን ልብስ ይሰጣቸው ዘንድ ፈቀደላቸው፡፡ አዛርያስ የተፈቀደለትን የታቦተ ጽዮን ልብስ ከአባቱ ከሊቀ ካህኑ ከሳዶቅ ተቀበለ፡፡ ከግምጃ ቤት ውስጥ እንጨት በመውሰድ ታቦተ ሙሴን አስመስሎ ታቦት አዘጋጀ፡፡ ያዘጋጀውን ታቦት ይዞ በሌሊት ወደ ቤተመቅደስ ገባ፡፡[105] የታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መሄድ ፍቃዷ ነበርና በሩ ተከፍቶ ታቦተ ጽዮን ከመሬት ከፍ ብላ ጠበቀችው፡፡ በቦታዋ ላይ አዲስ ያዘጋጀውን ታቦት አስቀምጦ የሙሴን ታቦት ይዞ ከምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጣ፡፡ ይህን ክስተት ደሴ ቀለብ ታሪክ ነገሥት በሚለው መጽሐፉ እንደሚከተለው ገልጾታል፤

> *… አዛርያስ ከንጉሱና ከአባቱ ዘንድ ገብቶ ወደ ባዕዳን አገር ከሰደዳችሁን ለእግዚአብሔር መስዋዕት የምንሰዋበት አንድ ነገር ከታቦተ ጽዮን ስጡን አለና ተናገረ፡፡ ሊቀ ካህኑና ንጉሱም ዕቃ ቤት ካለው ከታቦተ ጽዮን ልብስ እንሰጣችኋለን አሏቸው፡፡ ወቄት ወርቅ አወጡ፤ ከቤተ መቅደስም ሕንጻ የተረፈውን እንጨት መልካም መልካሙን ወስደው በታቦተ ጽዮን ቁመት ልክ ወርዱንም በወርዷ ልክ አድርገው ቀረፁት፤ ባወጡትም ወርቅ ለበጡት፡፡ … ካህናቱም ወደ ቤተመቅደስ ገብተው በእሷ አምሳል የተቀረጸውን ታቦት አኑረው ታቦተ ጽዮንን ሰርቀው ይዘው ሄዱ፡፡[106]*

ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮን ከእሱ ጋር እንደሆነች ያወቀው ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከገቡ በኋላ እንደሆነ ታሪኩ ያስረዳል፡፡[107] ወደ እናቱ መንግስት ደብረ ማክዳ ሲገባ ደማቅ አቀባበል ተደረገለት፤ እናቱም በክብር ተቀበለችው፤ በኢትዮጵያ ላይ አነገሰችው፡፡ በዚህም የሰሎሞን ስርዎ መንግስት በኢትዮጵያ ተጀመረ፡፡ ይህ ስርዎ መንግስት

[101] ደሴ ቀለብ፣ ገጽ 91
[102] ስርግው ገላው፣ ገጽ 34-9
[103] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 59
[104] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 31
[105] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 44
[106] ደሴ ቀለብ፣ ገጽ 102
[107] ስርግው ገላው፣ ገጽ 51

በደርግ መንግስት በጉልበት እስከተወገደበት ጊዜ ድረስ ለ3 ሺ ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ቦታ ይዞ ኖሯል፡፡ በዚህ ሂደት የመጀመሪያዎቹ እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ ገቡ፡፡ በንጉሱና በሊቀ ካህኑ አዛርያስ አማካኝነት እምነታቸውንና ባህላቸውን ለኢትዮጵያ አስተላለፉ፡፡ ኢትዮጵያም ከእስራኤል በመቀጠል የመጀመሪያዋ ሕገ ኦሪትን የተቀበለች አገር ሆነች፡፡ ንጉስ ሰሎሞንና ሊቀ ካህኑ ሳዶቅ ዋናው ታቦት እንደተወሰደባቸው ሲያውቁ በአዛርያስ የተሰራላቸውን ታቦት በተሻለ ሁኔታ አዘጋጁት፡፡ እንደ ክብረ ነገስት ገላጻ ንጉስ ሰሎሞን ታቦተ ጽዮን መሄዷን ካወቀ በኋላ የእስራኤልን ልጆች እንዲህ አላቸው፤

> *ክብራቸው ፈረሰ፤ እግዚአብሔርም ተዋቸው፤ ብለው ያልተገረዙት ወገኖች በላያችን ላይ እንዳይመኩ ተውት ከእንግዲህ በኋላ ለሌሎች ወገኖች አትግለጡ፤ እነዚህን የተጠጋጉና የተያያዙ ጠፍጣፋ ገበታዎች ግን አሁኑኑ እንቀድሳቸው፤ በወርቅም እንለብጣቸው፤ በጽዮን ምሳሌ እንሸልማቸው፤ በውስጡም የሕጉን መጽሐፍ እናስቀምጥ፡፡*[108]

አዛርያስም ታቦቱን ሲወስድ ከሁለቱ ጽላት አንዱን እና ሌሎችን ንዋያተ ቅድሳት እንደተወላቸው ይገመታል፡፡ ሌዋውያን ካህናት በምናሴ ዘመን ከቤተመቅደሱ ይዘውት ወደ ግብጽ የተሰደዱት ይህን በአዛርያስ የተሰራውንና በንጉስ ሰሎሞን በደንብ የተስተካከለውን ታቦት እና የተለያዩ ነዋያተ ቅድሳት እንደሚሆን መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ ይህ የበለጠ የሚያስረግጥልን የአይሁዶች ከግብጽ ኤሌፋንታይን ደሴት የተደረገ ስደት ወደ ኢትዮጵያ የሆነው ቀደምት አያቶቻቸው በኢትዮጵያ እንዳሉ መረጋገጡ ነው፡፡[109] ስለሆነም ክብረ ነገስት የሙሴን ታቦት ጉዞ ያስቀመጠልን ሲሆን የታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ ግን የአዛርያስን ታቦት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

ምርምሩ " ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት ጭብጦች ላይ የተደረገ ንጽጽራዊ ጥናት" ነዉ፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓለማ በሁለቱ መጸሕፍት መካከል ያለዉን አንድነት እና ልዩነት በማሳየት የትኛዉ ጭብጥ ይበልጥ አሳማኝ እንደሆነ በመረጃ አስደግፎ መግለጽ ነዉ፡፡ ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መካከል ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ በሁለቱ መጸሕፍት መካከል ያለዉ ልዩነት በምንድን ነዉ? የሚለዉ ይጠቀሳል፡፡ ጥናቱ በአይነታዊ የምርምር ስልት የቀረበ ሲሆን፤ የመረጃ ምንጩም ሰነድ ፍተሸ ነዉ፡፡ ከክብረ ነገስት እና ከታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት እንዲሁም ከርዕሰ ጉዳዮ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ የተለያዩ ሰነዶች ተለይተዉ፣ ተደራጅተዉ እና ተሰንደዉ በንጽጽራዊ ንድፈ ሀሳብ አማካኝነት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፊት መካከል አንድነትና ልዩነት ያለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሁለቱ መጻሕፍት ያላቸዉን ተመሳስሎ ስንመለከት፡-

- ✓ የሙሴ ታቦት ሲና በርሃ ላይ በሙሴ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ለእስራኤላዉያን የተሰጣቸዉ መሆኑን ሁለቱም መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርገው ያምናሉ፤

---

[108] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 64

[109] ጌታቸው ተስፋዬ፣ ገጽ 201-212

- ✓ የሙሴ ታቦት ከሙሴ እስከ ንጉስ ሰሎሞን ድረስ በልዩ ልዩ ቦታ ስትንቀሳቀስ ቆይታ ንጉስ ሰለሞን ባሰራዉ ቤተ መቅደስ ተቀምጣ መቆየቷን ሁለቱም ስራዎች የሀሳብ ስምምነት አላቸዉ፤
- ✓ የሙሴ ታቦት ከንጉስ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ መውጣቷን ሁለቱም ድርሳናት ያረጋግጣሉ፤
- ✓ ሁለቱም መጻሕፍት የሙሴ ታቦት ኢትዮጵያ ዉስጥ አክሱም መሆኗን ይስማማሉ፤ አሁንም ድረስ እዚያዉ እንዳለች ልዩነት የላቸዉም፡፡

ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ በክብረ ነገስት እና በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጻሕፍት መካከል ተመሳስሎ እንዳለ ሁሉ የሚከተሉት ልዩነቶችም አላቸው፡፡ የልዩነታቸዉ መነሻም የሙሴ ታቦት ከንጉስ ሰለሞን ቤተ መቅደስ በጠፋችበት ዘመን፣ ባወጧት ሰዎች፣ ወደ ኢትዮጵያ በመጣችበት መንገድ እና በተሰረቀችበት ምክንያት ይገለጻል፡፡ በመሆኑም፡-

- ✓ ከዘመን አንጻር ክብረ ነገስት የሙሴ ታቦት በ935 ቅልክ ከንጉስ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ እንደ ተወሰደች ሲገልጽ፤ በአንጻሩ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ ደግሞ በንጉስ ምናሴ ዘመን (ከ687-642 ቅልክ) መሆኑን ይገልጻል፤
- ✓ እንደ ክብረ ነገስት መጽሐፍ የሙሴን ታቦት ከንጉስ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ያወጣት/የሰረቃት የሳዶቅ ልጅ አዛሪያስ ሲሆን፤ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ ይዟት እንደመጣ ያትታል፡፡ በታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ ደግሞ የሙሴን ታቦት ያወጧት በምናሴ ዘመን በ670 አካባቢ የነበሩ ሌዋውያን ካህናት ሲሆኑ ወደ ግብጽ ኤሌፋንታይን ደሴት ይዘዋት እንደሄዱና ለ200 ዓመት በዚያ ቆይታ እንደገና በ470 ቅልክ አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ጣና ቂርቆስ ደሴት ለ800 ዓመት ቆይታ በ330 ዓ.ም ወደ አክሱም እንደሄደች ይገልጻል፡፡
- ✓ የሙሴ ታቦት ከንጉስ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ የወጣችበትን ምክንያት በተመለከተ ክብረ ነገስት የእስራኤል የበኩር ልጆች በንጉስ ሰለሞን አማካኝነት ከቀዳማዊ ምንልክ ጋር ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ሲወሰንባቸዉ፤ በዉሳኔዉ ቅር የተሰኙ ካህናት የሙሴን ታቦት አብረዉ ይዘዋት እንደሄዱ ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ ደግሞ በንጉስ ምናሴ ዘመን የንጉስ ሰለሞን ቤተ መቅደስ ሳይቀር ጣዖት ቆሞ ይመለክ ስለ ነበረ ሌዋውያን ካህናት የታቦቷን ከጣዖት ጋር አብሮ መቀመጥ በመቃወም ታቦቷን ይዘዉ ወደ ግብጽ ከንጉስ ምናሴ እንደ ሸሹ ያብራራል፡፡

የሁለቱ መጻሕፍት የልዩነት ምክንያት የታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ በሙሴ ታቦትና በአዛርያስ ታቦት መካከል ያለውን ልዩነት አለመረዳት ወይም አለማወቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ታቦታት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡና በአክሱም እንደሚገኙ መረጋገጡ ትልቅ ቁምነገር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመጻሕፍቱ ጋር አስረጅ ድርሳናትን በማጣቀስ ለመተንተን እንደተሞከረዉ ከሙሴ ታቦት መሰወር ጋር በተያያዘ የክብረ ነገስት አምክንዮ አሳማኝነቱ

ጎልቶ ይታያል፡፡ ስለሆነም ከሙሴ ታቦት መጥፋት ጋር በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለው አንድነት፣ ልዩነትና የልዩነታቸው ምክንያት በዚህ ጥናት ተለይቷል፡፡ ነገር ግን ሙሴ በደብረ ሲና የተቀበለው ሁለት ጽላት ስለነበር ሁለቱ ጽላት ከሙሴ ታቦት ጋር ይሁን ወይንም አንዱ ከሙሴ ታቦት አንደኛው ደግሞ ከአዛርያስ ታቦት ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥናት እንዲካሄድ ምክረ ሀሳብ በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውጤታማ ይሆን ዘንድ መጻሕፍትን በማዋስና ሙያዊ አስተያይት በመስጠት ያገዙንን አቶ ምንዋጋው ተመስገን ከልብ እናመሰግናለን፡፡

## 7. ዋቢ ጽሑፎች

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/የሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ (2001)፡፡ ሐመረ ተዋሕዶ፤ የሐመር መጽሔት ልዩ እትም፡፡ አዲስ አበባ፤ አማኑኤል ማተሚያ ቤት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ (፳፻)፡፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡

ሣህለ ጥላሁን፡፡ (1999) ፡፡ ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን?፡፡ አዲስ አበባ፤ (አሳታሚው ያልገለጸ)፡፡

ስርግው ገላው፡፡ (1994) ፡፡ ክብረ ነገስት ግዕዝና አማረኛ፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደስላሴ፡፡ (1999)፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ብርሃኑ ጎበና፡፡ (1990)፡፡ ዓምደ ሃይማት፡፡ አዲስ አበባ፤ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለጻድቅ መኩሪያ፡፡ (2013) ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፡፡ አዲስ አበባ፤ ታሪክ አሳታሚ፡፡

ቸርነት አበበ፡፡ (2014)፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ፤ Printed @ Eclipse.

አስረስ ያየህ፡፡ (1989)፡፡ ቤተእስራኤል በኢትዮጵያ ታሪካቸው፣ ባህላቸውና አኗኗራቸው፡፡ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አባ ጎርጎርዮስ (የሸዋ ሊቀ ጳጳስ)፡፡ (2014)፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን፡፡ (፲፱፻፹፰)፡፡ ወንጌል ቅዱስ፤ ንባቡና ትርጓሜው (አንድምታ)፡፡ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998 ዓ.ም)፡፡ "የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር"፡፡ ፣ ባህር ዳር፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ደሴ ቀለብ፡፡ (፳፻፪)፡፡ ታሪከ ነገሥት፡፡ አዲስ አበባ፤ በኢት/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡ (2000)፡፡ ትንቢተ ዳንኤል ከዘመነ ባቢሎን እስከ ዓለም ፍጻሜ፡፡ አዲስ አበባ፤Commercial Printing Press.

**ጌታቸው ተስፋዬ። (1999)። ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ። አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር።**

Leeman, B. (2009). The Sabaean Inscriptions at Adi Kaweh-Evidence Supporting the Narrative of The Sheba-Menelik Cycle of the Kebra Nagast.

Leeman, B. (2010). The Ark of The Covenant: Evidence Supporting the Ethiopian Tradiations (www.queen-of-sheba-university.org

Hancock, G. (1997). The Sign and The Seal፡ the Quest for the Lost Ark of the Covenant. Great Britain: arrow Books Press.

Brooks, M. F. (2000). Kebra Nagast: The True Ark of the Covenant. Asmara: The Red Sea Press, Inc.